# የአስኮ ቃለ ህይወት ቤተክርስቲያን

# የአባላት መመዝገቢያ ሲስተም

# የአጠቃቀም መመሪያ

የካቲት 2014ዓ.ም

## ማውጫ


መግቢያ ........ 3

የሲስተሙ አወቃቀር ........ 4

በሲስተሙ መከወን የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራትና መግለጫዎች ........ 5

1. ወደ ሲስተሙ መግቢያ ........ 5
2. ጠቅላላ መረጃ ........ 5
3. አዲስ አባል መመዝገቢያ ........ 5
4. የአባላት መረጃ ማስተካከያ ........ 6
5. የአባላት ዝውውር ........ 6
6. የአባላት ጉብኝት ........ 7
7. የአባላት ሰርተፍኬት ማዘጋጃ ........ 7
8. የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ........ 7
9. አገልግሎት ዘርፎች ........ 8
10. የመረጃ ዴስክ ........ 8
11. የአባላት ሪፖርት ........ 9
12. ጠቅላላ የአባላት መረጃ ........ 10
13. የአገልጋዮች የአባላት ምድብ ሪፖርት ........ 10
14. የአባላት የጉብኝት ሪፖርት ........ 10
15. ማስተካከያዮች ........ 10
16. ስለሲስተሙ መረጃ ........ 11
17. አካውንት መቆጣጠሪያ ........ 11

ማጠቃለያ ........ 12



Copyright ©2022 All rights reserved

## መግቢያ


የቤተክርስቲያን አባላት ማደራጃ ሲስተም ቤተክርስቲያናት የአባላቶቻቸውን መረጃ በተደራጀ እና ወጥነት ባለው መልኩ እንዲይዝና አባሎቶቻቸውን መረጃ በሚገባ መልኩ በመያዝ መከታተል እንዲችሉ ለማገዝ የተሰራ ሲስተም ሲሆን በዋናነት ስድስት ተግባራትን ለመከወን ያስችላል። ሲስተሙን የማበልፀግ ስራ ቀጣይነት ያለው ሲሆን በቅርብ ጊዜያት ውስጥ የአባላት የክፍያ ሁኔታ፣ የአባላት ቤተሰባዊ ትስስሮሽ ማሳያ፣ የቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ የቤተክርስቲያን ወጪና ገቢ እንዲሁም የአባላት የመማማሪያ መንገድ የሚካተትበት ይሆናል።

አምስቱ ተግባራት

I. የአባላት መረጃ ማደራጀት
   i. አዲስ አባል መመዝገብ
   ii. የአባላት መረጃ ማስተካከል
   iii. የአባላት ዝውውር
   iv. የአባላት ጉብኝት
   v. የአባልነት ሰረተፍኬት ማዘጋጀት
II. የአባላት የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት/የቤት ህብረት መረጃ ማደራጃ
   i. አዲስ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት/የቤት ህብረት ቡድኖችን መመስረት
   ii. አባላትን በየመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት/በየቤት ህብረቱ መመደብ
   iii. የአባላት የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት/የቤት ህብረት ስርጭትን መከታተል
   iv. በመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት/የቤት ህብረት ውስጥ የታቀፉ እና ያልታቀፉ አባላት ዝርዝር መመልከት
III. የአባላት የአገልግሎት ዘርፍ መረጃ ማደራጃ
   i. አዲስ የአገልግሎት ዘርፎችን ማስጀመር
   ii. አባላትን ወደ የአገልግሎት ዘርፎች ምድባ መስራት
   iii. በአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ የታቀፉ እና ያልታቀፉ አባላት ዝርዝር መመልከት
   iv. በተለያዩ ወቅቶች ያገለገሉ የአባላት ዝርዝር በቀላሉ ማግየት
IV. የአባላት ጉብኝት ክትትል
   i. የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በእነርሱ ስር የተመደቡ አባላትን በቀላሉ መለየት ያስችላል
   ii. የቤተክርስቲያኒቱ አባላት የጉብኝት መረጃ መመዝገብ
   iii. አባላቱ በጉብኝቱ ወቅት ያሉበትን ሁኔታ መመዝገብ እና ሪፖርት ማሳየት
   iv. የተለያዩ የጉብኝት ሪፖርቶችን ማሳየት
V. ልዩ ልዩ ሪፖርቶች
   i. ዝርዝር እና ወቅታዊ የአባላት ሪፖርት
   ii. የአባላት ግለታሪኮች(ግላዊ መረጃ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት/የቤት ህብረት መረጃና የአገልግሎት ታሪክ መረጃ)
   iii. የአባላት የመኖርያ አካባቢ ስርጭት
   iv. ወቅታዊ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት/የቤት ህብረት ምድቦች እና የአገልግሎት ዘርፎች ሁኔታ ሪፖርት

Copyright ©2022 All rights reserved

# የሲስተሙ አወቃቀር




Copyright ©2022 All rights reserved
W360 Church Management System
http://tco21.wordpress.com/

## በሲስተሙ መከወን የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራትና መግለጫዎች

### 1. ወደ ሲስተሙ መግቢያ

- ወደ ሲስተሙ ለመግባት የኢሜል አድራሻ(email address) እና የይለፍ ቃል(password) ሊኖር ያስፈልጋል።
- ወደ ሲስተሙ ለመግባት የሚጠቀሙበት መለያ ለሁሉም ሰው የተለያየ ይሆናል።
- የሚጠቀሙት የይለፍ ቃል በተቻለ መጠን ቀላል ባይሆን ይመከራል።
- የይለፍ ቃሎን ቢዘነጉ የሲስተሙን አስተዳዳሪ ያናግሩ።

### 2. ጠቅላላ መረጃ

- ይህ ገፅ ወደ ሲስተሙ ያስገባነውን ዋና ዋና መረጃዎች ተጠናክረው የምናይበት ገፅ ሲሆን በዚህ ገፅ ላይ ከምናገኛቸው መረጃዎች መካከል
    - ቋሚ የአባላት ብዛት
    - ወደ ጌታ የሄዱ የአባላት ብዛት
    - የአባላት የዝውውር መረጃ
    - ከጌታ ቤት የወጡ የአባላት ብዛት
    - የወንዶች የአባላት ብዛት
    - የሴት የአባላት ብዛት
    - የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ብዛት
    - ባለፈው ወር የተመዘገቡ የአባላት ብዛት
    - የቤተክርስቲያኒቱ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ዝርዝር
    - ወቅታዊ የቤተክርስቲያቢቱ ዜናዎች እና ማስታወቂያዎች ይገኙበታል

### 3. አዲስ አባል መመዝገቢያ

- እዚህ ገፅ ላይ በቤተክርስቲያኒቱ የአባላት ባህር መዝገብ ላይ ለመመዝገብ መስፈርቱን አሟልተው ብቁ የሆኑ አባላት የሚመዘገቡበት ገፅ ሲሆን አባሉን መፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ወይም የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ ከመመደባችን አስቀድመን እዚህ ቦታ መመዝገብ ያስፈልጋል።
- አንድን አባል ወደሲስተሙ ከመመዝገባችን በፊት አስቀድመን የተሟላ መረጃ እጃችን ላይ መኖሩን እርግጠኛ መሆናችንን እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል።
- እያንዳንዱ አባል ወደሲስተሙ በሚመዘገብበት ወቅት አባሉን የሚከታተል አገልጋይ መመደብ ይኖርበታል።
- የመኖርያ አካባቢ ወይም የስራ አካባቢ ከተዘረዘሩት ውጪ በሚሆንበት ጊዜ የሲስተሙ ማስተካከያ ገፅ ላይ በመሄድ መጨመር ይቻላል።

Copyright ©2022 All rights reserved

- የአባሉን ኢሜል አድራሻ ማግኘት በማይቻልበት ወቅት ለጋራ አገልግሎት የተከፈተውን መጠቀም ይቻላል - askomember@gmail.com
- የይለፍ ቃል የተጨመረው ሲስተሙ በቀጣይ ሲበለፅግ ለእያንዳንዱ አባል መለያ ለመፍጠር ታስቦ ስለሆነ ለጊዜው 12345 መጠቀም ይቻላል።
- የተዘረዘሩት የአካባቢ መጠሪያዎች በቂ ሆነው ካልተገኙ ማስተካከያዮች የሚለው ገጽ ላይ በመሄድ ማስተካል ይቻላል።

## 4. የአባላት መረጃ ማስተካከያ

- የተሳሳቱ ወይም መለወጥ የሚገባቸውን የአባላት መረጃ ለማስተካከ የሚረዳ ገፅ ነው።
- ከላይ ተዘርዝረው የምናገኛቸው የቀለም ጠቋሚዎች  አንድን አባል በቀላሉ ፈልገን እንድናገኝ የሚረዱ ናቸው። በዚህም መሰረት
  - i. ቋሚ አባላት - አረንጓዴ
  - ii. ወደ ጌታ የሄዱ አባላት - ቡኒ
  - iii. ከጌታ ቤት የወጡ አባላት - ቀይ
- ከላይ በሚገኘውም መፈለጊያ ሳጥን የምንፈልገውን አባል መረጃ በማስገባት በፈለግ እንችላለን
- ከላይ በአረንጓዴ ሳጥን ውስጥ አባሉ ያለበትን ሁኔታ መለወጥ ያስችለናል። ሌሎችንም መረጃዎች በተመሳሳይ መንገድ መለወጥ እንችላለን።

## 5. የአባላት ዝውውር

- እዚህ ገጽ ላይ በዋናነት የአባሉን ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን መዘዋወርን ወይም አባሉ ከሌላ ቤተክርስቲያን የመጣ መሆኑን የምንመዘግብበት ስፍራ ነው።
- ይህን ገጽ ስንከፍት ሁለት ጠቋሚዎችን እንመለከታለን
  - i. አቅጣጫውም እንደሚጠቁመው አንድን አባል ከሌላ ቤተክርስቲያን ለመቀበል የሚያገለግል ሲሆን
  - ii. ይሄ ደግሞ አንድን አባል ወደሌላ ቤተክርስቲያን ለማዘዋወር የሚጠቅመን ነው
- በሁለቱም ሁኔታዎች የሚዘዋወርበትን ቤተክርስቲያን መረጃ በአግባቡ መያዝ ያስፈልጋል እንዲሁም የዝውውሩን ቀንንም መመዝገብ ተገቢ ነው።

Copyright ©2022 All rights reserved
W360 Church Management System
http://tco21.wordpress.com/

## 6. የአባላት ጉብኝት

- ይህ ገጽ የአባላትን ክትትል መረጃዎች ለማጠናከር የተዘጋጀ ሲሆን ፊት ለፊት ያለው ገጽ ጠቅለል ያሉ መረጃዎችን ለምሳሌ ባለፈው ወር የተከናወነ የአባላት ጉብኝት፣ ባለፉት ሶስት ወራት የተከናወነ የአባላት ጉብኝት፣ ባለፈው ስድስት ወር የተከናወነ ጉብኝት እና በአንድ አመት የተከናወነ የአባላት ጉብኝት።
- እያንዳንዱ አገልጋይ የጉብኝቱን መረጃ በቀላሉ ማስገባት ይችላል። ይህን መረጃ በሚያስገባበት ወቅት የጉብኚውን ስም፣ የተጉብኚውን ስም፣ የጉብኝቱን ቀን፣ በጉብኝቱ ወቅት የተገኘውን መረጃ እንዲሁም በልዩ መልኩ ድጋሚ ጉብኝት የሚያሻው እንደሆነ መጠቆም ያስችላል። ሲስተሙም በልዩ መልኩ ድጋሚ ጉብኝት የሚያሻቸውን አባላት ለይቶ ያሳየናል።
- እያንዳንዱ አገልጋይ በስሙ ትይዩ ያለውን መጠቆሚያ በመንካት ያከናወናቸውን ጉብኝቶች ማየት ይችላል

## 7. የአባላት አስራት ክፍያ መከታተያ

### 7.1. የአስራት ክፍያ መመዝገቢያ

- የወርሃዊ ክፍያ በተፈፀመ ወቅት መረጃውን ለመመዝገብ ያገለግላል።

### 7.2. የአስራት ክፍያ መከታተያ

- ላለፉት ሶስት፣ ስድስት እና ከአንድ አመት በላይ የአስራት ክፍያ ያልፈፀሙ የአባላት ዝርዝርን ለማየት ይረዳል።

### 7.3. የአስራት ሪፖርት

- የአስራት ገቢን ሂሳባዊ ሪፖርት ለማየት ያግዛል።

## 8. የአባላት ሰርተፍኬት ማዘጋጃ

- ለምሳሌ እንዲሆን የተዘጋጀ የአባልነት ሰርተፍኬት ሲሆን ለእያንዳንዱ አባል ታትሞ መሰጠት የሚቻል ነው።
- ሰርተፍኬቱ ላይ የሚፈርሙ አካላትን ስም መምረጥ እንችላለን።

## 9. የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት

### 9.1. አዲስ የጥናት ቡድን

- መፅሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን የሚመራው አካል የጥናት ቡድኖችን ያደራጅ እና የጥናት ቡድኖችን መረጃ እዚህ ገጽ ላይ ማስገባት ይቻላል።
- እያንዳንዱ የጥናት ቡድን የተለያየ ስም ይኖረዋል
- የጥናት ቡድኑን መረጃ ማስተካከል ይቻላል

Copyright ©2022 All rights reserved
W360 Church Management System
http://tco21.wordpress.com/

### 9.2. የጥናት ቡድን መመደቢያ

- እዚህ ገጽ ላይ አባላትን በየጥናት ቡድኑ መመደብ ያስችለናል
- ከላይ እንደምንመለከተው ሁለት ጠቋሚዎች ያሉ ሲሆን አባላትን ጥናት ቡድን ውስጥ የተመደቡ እና ያልተመደቡ ተብሎ መክፈል ያስችለናል።
- አንድ አባል በጥናት ቡድኖች ውስጥ ሲመደብ ሶስት አይነት ድርሻ ሊኖረው ይችላል
  - አስጠኚ - ክፍሉን በሃላፊነት የሚመራ እና የክፍሉ ተጠሪ የሚሆን
  - ምክትል አስጠኚ - ከአስጠኚው ጋር በመተባበር ጥናት ክፍሉን የሚመራ
  - አጥኚ - የጥናት ክፍሉ አባላትን ይወክላል
  - አጋር - ለተወሰነ ጊዜ ተመድበው የሚያጠኑ አባላትን ይወክላል
- አንድ አባል አንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ላይ ብቻ ነው መመደብ የሚችለው።

## 10.አገልግሎት ዘርፎች

### 10.1. አዲስ አገልግሎት ዘርፍ

- የአገልግሎት ዘርፎች መረጃ ለማደራጀት ያግዘናል

### 10.2. አገልግሎት ዘርፍ መመደቢያ

- በዚህ ገጽ አማካኝነት አባላትን በየአገልግሎት ዘርፎቹ መመደብ የሚያስችለን ሲሆን አንድ አባል ከአንድ በላይ የአገልግሎት ዘርፍ ላይ ሊመደብ ይችላል።
- አባላትን በየአገልግሎት ዘርፎች በምንመድብበት ወቅት ያላቸውንም ኃላፊነት አብረን መጨመር እንችላለን።

### 10.3. የአገልግሎት ዘርፍ ታሪካዊ መረጃ

- በዚህ ገጽ ውስጥ የምናገኘው መረጃ በምንመርጠው የአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ አገልግሎቱ ከተጀመረ ጀምሮ ያገለገሉ አባላትን ዝርዝር የሚያሳየን ሲሆን ይህን መረጃ እንደአስፈላጊነቱ ለቤተክርስቲያን ታሪክ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

## 11.የመረጃ ዴስክ

### 11.1. የአባላት ግለ ታሪክ

- የአንድን አባል ሙሉ መረጃ የምናገኝበት ገጽ ነው
- የመረጥነውን አባል የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲሁም የአገልግሎት መረጃ ያሳየናል

Copyright ©2022 All rights reserved

### 11.2. የአባላት የመኖሪያ አካባቢ ስርጭት

- የአባላትን የመኖርያ አካባቢ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የስርጭቱ መረጃ የሚያሳይን ገጽ ነው።
- ይህን መረጃ የሰፈር የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ምድቦችን ለማደራጀት ልንጠቀምበት እንችላለን።
- በተጨማሪም ይህን መረጃ ለአባላት ጉብኝት ሊጋዥ አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን።

### 11.3. ስለመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ምድቦች

- የእያንዳንዱን የጥናት ቡድኖች አወቃቀር እና የአባላት ምድብተኞች የምናይበት ገጽ ነው።
- የየመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ምድብ አስጠኚዎችንና ምክትል አስጠኚዎችን በቀላሉ እንድናውቅም ይረዳናል።

### 11.4. ስለአገልግሎት ዘርፎች ምድብ

- የእያንዳንዱን የአገልግሎት ዘርፎች አወቃቀር እና የአባላት ምድብተኞች የምናይበት ገጽ ነው።
- የየአገልግሎት ዘርፎች ሰብሳቢዎችና ምክትል ሰብሳቢዎች እንዲሁም ዋና ፀሃፊዎችን በቀላሉ ስልክ ቁጥራቸውን ጨምሮ ያሳየናል

## 12.የአባላት ሪፖርት

### 12.1. ወቅታዊ የአባላት ሪፖርት

- በዚህ ክፍል ውስጥ ሶስት ዋና ዋና ነገሮችን እናገኛለን
  - 11.1.1 **የአባላት ወቅታዊ ሪፖርት** - ፊትለፊት በምናገኘው የመምረጫ ሳጥን ውስጥ የሪፖርት መነሻ እና የመጨረሻ ቀን አስገብተን ሪፖርት አሳይ የሚለውን በምንጫንበት ወቅት ሲስተሙ በተጠቀሰው ቀን ውስጥ በቤተክርስቲያኒቱ ያሉ ቋሚ አባላት ብዛት፣ በተጠቀሰው ቀን በዝውውር ከሌላ ቤተክርስቲያን የመጡ አዳዲስ አባላት ብዛት፣ በተጠቀሰው ቀን አዲስ የተጨመሩ የአባላት ብዛት፣ በተጠቀሰው ቀን ከቤተክርስቲያኒቱ ወደሌላ አጥቢያ የተዘዋወሩ የአባላት ብዛት እንዲሁም በተጠቀሰው ቀን ወደ ጌታ የሄዱ የአባላት ብዛት እና በተጠቀሰው ቀን ወደኋላ የተመለሱ የአባላት ብዛት በዝርዝር የሚያሳየን ይሆናል።
  - **የመፅሐፍ ቅዱስ ወቅታዊ ሪፖርት** - በዚህ ገጽ ውስጥ የምናገኘው መረጃ በዋናነት በአሁኑ ወቅት በቤተክርስቲያን ወስጥ የለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት የተመለከተ መረጃ ሲሆን በዚህ ገጽ ተካቶ ከምናገኛቸው መረጃዎች መካከል በአሁን ሰአት ያሉ ቋሚ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ምድቦች ብዛት፣ በጥናት ምድቦች ታቅፈው የሚያጠኑ የቋሚ የአባላት ብዛት፣ በጥናት ምድቦች ያልታቀፉ የቋሚ የአባላት ብዛት፣ አባላት የተመደቡባቸው የጥናት ምድቦች ብዛት እንዲሁም አባላት ያተመደቡባቸው የጥናት ምድቦች ብዛት ይገኙበታል። ከዚህም በመቀጠል የአስጠኚዎች ብዛት፣ የምክትል አስጠኚዎች ብዛት፣ የአጥኚዎች ብዛት፣ የአጋር አጥኚዎች ብዛት፣ በቅርብ ጊዜያት

Copyright ©2022 All rights reserved
W360 Church Management System
http://tco21.wordpress.com/

የተቋቋሙ የጥናት ምደቦችን ለይተን መመልከት እንድንችል ያስችለናል። በስተመጨረሻም የአስጠኚዎች ዝርዝር፣ የምክትል አስጠኚዎች ዝርዝር እንዲሁም የቋሚ የጥናት ምድቦች የአካባቢ ስርጭት መረጃዎች ተዘርዝረው ማግኘት እንችላለን።

- **የአገልግሎት ዘርፎች ወቅታዊ ሪፖርት** - ከዚህ ገጽ የምናገኘው መረጃ ወቅታዊ የአገልግሎት ዘርፎች ሪፖርት ሲሆን ይህም በአሁን ወቅት ያሉ የአገልግሎት ዘርፎች ብዛት፣ በአገልግሎት ዘርፎች ተመድበው የሚያገለግሉ አባላት ብዛት፣ የአገልግሎት ዘርፍ ወስጥ ያልተመደቡ አባላት ብዛት እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፎች ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሃፊዎችን ዝርዝር ማየት ያስችለናል።

## 13.ጠቅላላ የአባላት መረጃ

- በዚህ የሪፖርት ገጽ በቤተክርስቲያኒቱ ያሉትን አባላት የተመለከቱ መረጃዎች በዝርዝር የሚቅርቡ ሲሆን ከእነሱም መካከል የቋሚ አባላት የትዳር ሁኔታ ስርጭት፣ የቋሚ አባላት የፆታ ስርጭት፣ የቋሚ አባላት የትምህርት ደረጃ ስርጭት፣ የቋሚ አባላት የትምህርት አይነት ስርጭት፣ የቋሚ አባላት የጌታ ቤት ቆይታ ስርጭት፣ የቋሚ አባላት የእድሜ ስርጭት እና የቋሚ አባላት የአካባቢ ስርጭት።
- ከዚህ ከምናገኘው መረጃ ተነስተን ጠቃሚ ትንታኔዎችን ማዘጋጀት እንችላለን።

## 14.የአገልጋዮች የአባላት ምድብ ሪፖርት

- ይህን ገጽ ስንከፍት ከምናገኘው የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ዝርዝር ውስጥ አንዱን ስንመርጥ በመረጥነው አገልጋይ ስር የተመደቡትን እና ክትትል የሚደያደርግባቸው የአባላት ዝርዝር ማየት እንችላለን።

## 15.የአባላት የጉብኝት ሪፖርት

- በዚህ ገጽ የተካተቱ መረጃዎች የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ያከናወኑትን የአባላት ጉብኝት የተዘረዘረ ሲሆን በተጨማሪም በእያንዳንዱ አገልጋይ የተከናወነውን የጉብኝት ብዛት ያሳያል።
- ከዚህም ባለፈ ባለፈው ወር የተከናወነ የአባላት ጉብኝት ብዛት፣ ባለፈው ሶስት ወር የተከናወነ የአባላት ጉብኝት ብዛት፣ ባለፈው ስድስት ወር የተከናወነ የአባላት ጉብኝት ብዛት እና በአንድ አመት የተከናወነ የአባላት ጉብኝት ብዛት ተዘርዝረው እናገኛለን።
- ከታች ባለው ክፍል ደግሞ በቅርብ ጊዜያት ድጋሚ ጉብኝት የሚያስፈልጋቸው የአባላት ዝርዝር መመልከት እንችላለን።

## 16.ማስተካከያዎች

Copyright ©2022 All rights reserved
W360 Church Management System
http://tco21.wordpress.com/

### 16.1. ማስታወቂያና ዜናዎች

- በዚህ ገጽ ላይ ሁለት ተግባራትን መከወን እንችላለን። የመጀመሪያው የቤተክርስቲያኒቱን ማስታወቂያና ዜናዎችን ወደሲስተም ማስገባት ሲሆን ሁለተኛው ያስገባነው መረጃን መመልከት እና የሚስተካከሉ መረጃዎች ካሉም ማስተካከል ያስችለናል።
- እዚህ ቦታ የምንናስገባቸውን ማስታወቂያዎችና ዜናዎች ወደሲስተሙ ስንገባ በምናገኘው የመነሻ ገጽ ላይ የምናገኛቸው ይሆናል።
- በቀጣይ ሲስተሙ ለአባላት ክፍት በሚሆንበት ወቅት ለአባላትም የሚታይ ይሆናል።

### 16.2. የአድራሻ መረጃ ማስተካከያ

- በዚህ ገጽ የተዘረዘሩትን መረጃዎች በመሙላት በሲስተሙ ውስጥ የምንጠቀማቸውን አድራሻዎች መመዝገብ እንችላለን።
- እነዚህን መረጃዎች የአባላቱን የመኖርያ አካባቢ፣ የአባላቱን የስራ አካባቢ እንዲሁም መፅሐፍ ቅዱስ ጥናት አካባቢዎችን ለማስገባት እንጠቀምበታለን።

### 16.3. የቤተክርስቲያን መረጃ ማስተካከያ

- ዋና ዋና የቤተክርስቲያን መረጃዎችን የምናስተካክልበት ገጽ ነው።

## 17.ስለሲስተሙ መረጃ

- ስለሲስተሙ መሰረታዊ መረጃዎች የምናገኝበት ገጽ ሲሆን ሲስተሙ በቀጣይ የሚያካትታቸውን ስራዎች ይጠቅሳል።
- በተጨማሪም ስለሲስተሙ አጠቃቀም መመሪያ የምናገኝበት ገጽ ነው።

## 18.አካውንት መቆጣጠሪያ



ይህ ምልክት የአካውንታችንን መረጃዎች ማስተካከል ያስችለናል



ይህ ምልክት የአካውንቶን የይለፍ ቃል መቀየር ያስችላል

ሌሎች ተቆጣጣሪ(Admin) አካውንቶችን እንድንፈጥር ያስችለናል



ይህ ምልክት አካውንቶን ዘግተው የሚወጡበት ምልክት ሲሆን ሁልጊዜም ቢሆን ሲስተሙን ተጠቅመው ስንጨርስ ይህንን መጫን መዘንጋት አይኖርብንም

Copyright ©2022 All rights reserved
W360 Church Management System
http://tco21.wordpress.com/

## ማጠቃለያ

ለኢትዮጵያ አጥቢያ ቤተክርስቲያኖች የተሰራ ሲስተም ሲሆን ቤተክርስቲያናት የአባላቶቻቸውን መረጃ በተደራጀ መልኩ ለመያዝ እና የአባሎታቸውን የአገልግሎት ሁኔታ ከመፅሐፍ ቅዱስ የጥናት ምድብ ታሪካቸው ጋር በማስተሳሰር የተዋጣ የመረጃ ስርዓት እንዲኖር ይረዳል፡፡ይህ ቤተክርስቲያናት የአባላቶቻቸውን መረጃ በተደራጀ እና ወጥነት ባለው መልኩ እንዲይዙና አባሎቶቻቸውን መረጃ በሚገባ መልኩ በመያዝ መከታተል እንዲችሉ ለማገዝ የተሰራ ሲስተም ሲሆነ በዋናነት ስድስት ተግባራትን ለመከወን ያስችላል። ሲስተሙን የማበልፀግ ስራ ቀጣይነት ያለው ሲሆነ በቅርብ ጊዜያት ውስጥ የአባላት የክፍያ ሁኔታ፣ የቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ የቤተክርስቲያን ወጪና ገቢ እንዲሁም የአባላት የመማማሪያ መንገድ የሚካተትበት ይሆናል።

Copyright ©2022 All rights reserved